# Statewide Specialist Clinical Consultation Service

*A service provided by the Queensland Transcultural Mental Health Centre*

## Consumer information sheet (Amharic)

### የኩዊንስላንድ ሁሉንአቀፍባህል የአእምሮ ጤና ማእከል

## ሁሉንአቀፍባህል የህክምና አመክሮ አገልግሎት

## የባለጉዳይ መረጃ ዝርዝር

ቀደም ሲል በሁሉንአቀፍባህል የህክምና አመክሮ አገልግሎት፤ ሁለት ቋንቋ መናገር ከሚችል የአእምሮ ጤና አማካሪ ጋር ተነጋግረዋል።

ሁለት ቋንቋ የሚናገረው የአእምሮ ጤና አማካሪ ስም________________________________ ነው።

የሁሉንአቀፍባህል የህክምና አመክሮ አገልግሎት የሚከተሉትን አገለግሎቶች ሁለት ቋንቋ የመናገር ችሎታ ባላቸው አማካሪዎች አማካኝነት ይሰጣል።

- አግባብ ያላቸው ባህላዊ ግምገማዎች፤
- ከእርስዎ የአእምሮ ጤና ጉዳይ ጋር በማዛመድ በባህላዊ ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ ማድረግ፤
- የግለዎን የጤና እንክብካቤ በሚመለከት እቅድ ማውጣት፤ ወይንም ቀደም ብሎ የተዘጋጀውን የማስተካከል እርዳታ መስጠት፤
- ስለ አእምሮ ጤና ጉዳይ ለእርስዎና ለተንከባካቢዎ መግለጫና ትምህርትን አስመልክቶ የአጭር ጊዜ እርዳታ ማድረግ ናቸው።

**<u>መብትዎ</u>**

የሚከተሉት መብቶች አለዎት፤

- ስለግል የጤና እንክብካቤዎ መወሰን
- በባህልዎ፤ በእድሜዎ፤ በኑሮ ደረጃዎ፤ በፆታዎ፤ በፆታ ምርጫዎ፤ በሃይማኖትዎ ወይንም ባለዎት የፖለቲካ አመለካከት አድልዎ ሳይደረግብዎ የባለሙያ እርዳታ ማግኘት፤
- ስለሁኔታዎ ወይንም ስለ በሽታዎ፤ በሚገባዎት ቋንቋ እንዲነገርዎት የማድረግ፤
- የሚረዳዎትን ግለሰብ (ጓደኛ፤ ዘመድ ወይንም የድጋፍ ሠራተኛ) እንክብካቤዎን በተመለከተ የማሳተፍ፤
- ግለኝነትዎንና ምስጢርዎን የማስከበር፤
- አስፈላጊ ከሆነ፤ አስተርጓሚ እንዲሰጥዎ የመጠየቅ፤
- በሚደረግልዎት ማንኛውም እንክብካቤ ካልረኩ አቤቱታ የማቅረብ መብቶች ናቸው።

**<u>ሃላፊነትዎ፤</u>**

ከአእመሮ ጤና ባለሙያዎች ጋር በመተባበር እየሠሩ የአእምሮ ጤና እንክብካቤዎን ለመጠበቅ የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይበረታታሉ፤

- ጤናዎን በተመለከተ የሚጠየቁትን ጥያቄዎች በተቻለ መጠን በግልፅ መመለስ፤
- ቀጠሮዎን ማከበር፤ ማክበር ካልቻሉ ደግሞ የጤና ሠራተኛውን መምጣት ያለመቻልዎን ቀደም ብለው መንገር፤
- ህክምናውን ወይንም የህክምንናውን ክንውን በስምምነቱ መሠረት መከታተል። ካልተቻለም፤ ህክምናውን ለምን መከታተል እንዳልቻሉ ለጤና ሠራተኛው መንገር።
- ለጤና እንክብካቤ ሠራተኛው፤ ለተመሳሳይ ችግር ሌላ የጤና እንክብካቤ ሠራተኛ ያዩ እንደሆነ መንገር ናቸው።

ተጨማሪ መረጃ ወይንም ስለገጠመዎት ስጋት ወይንም አቤቱታ ለማድረግ ከፈለጉ፤ የህክምና አገልግሎት አስተባባሪውን ወይንም የኩዊንስላንድ ሁሉንአቀፍባህል የአእምሮ ጤና ማእከል አስተዳዳሪን በስልክ ቁጥር (07) 3167-8333 ወይንም 1800 188 189 (ከብሪዝበን ከተማ ውጭ ከሆኑ) አለበለዚያም በ tccs@health.qld.gov.au የኢሜል መልእክት ይላኩልን።

እንግሊዘኛ መናገር ካልቻሉ 13 14 50 በመደወል ቋንቋዎን የሚናገር አስተርጓሚ በመጠየቅ (07) 3167 8333 እንዲደውሉ ያስደርጉ። (የአስተርጓሚው ክፍያ በማእከሉ ይሸፈናል)